# ሶሻል ዴሞክራሲ
# ርዕዮተ - ዓለም

# <u>ሶሽያል ዴሞክራሲ መመሪያ ርዕዮተ-ዓለማችን ነው</u>

## I. ርዕዮተ-ዓለም ምንድን ነው?

ግለሰቦች፣ አንድ የኅብረተሰብ-ክፍል ወይንም መደብ፣ አንድ ቡድን ወይንም ድርጅት ዕምነታቸውንና አመለካከታቸውን የሚገልጹበት የሃሳብና ምጥቀት-ያለው-ዓላማ መድብል (Body of Ideas & Ideals) ሲሆን፤ በተለይም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፖሊሲዎችንና ንድፈ-ሃሳቦችን ከማኅበረሰባዊ አንደምታቸውና ባህላዊ ገጽታቸው ጋር በማካተት ተዋናዮ ኅብረተሰብ የሚገኙበትን ታሪካዊ ሁኔታና ወቅትም ገላጭና የጉዞ አቅጣጫንም አመላካች ነው።
ከኅብረተሰብ ዕድገትና ብዙ-ጎንዮሽ ለውጥ ጋር የሚጣጣም ማሻሻያም ያደርጋል።

## II. የተለያዩ ርዕዮተ-ዓለሞች ታሪካዊ አመጣጥ ባጭሩ

የሰው ልጅ እያደገ በመጣ ማኅበራዊ ትስስርና መስተጋብር ላይ የተመሠረተ፣ አንጻራዊ በሆነ ደረጃም የተደራጀ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎችም ያሉት ህይወትን ነው የሚመራው። የተለያዩ ግንኙነቶችን ሥርዓት ካላበጀላቸው ያበጀውንም ሥርዓት በየጊዜው ሊያሻሽለው ካልቻለ ህይወቱ ይዛባበታል። ፈላጭና ቆራጭ ንጉሶች ወይንም ሌሎች አምባገነኖች በሚገዟቸው ኅብረተሰቦች/ሀገሮች ዉስጥ ለተወሰኑ ዓመታት ወይም ዘመናት ሕዝብ ጭጭ ብሎ እንዲገዛ እንደሚደረግ ቢታወቅም ኅብረተሰቡ በቁጥር እየተበራከተ፣ ፍላጎቶቹ እየሰፉ፣ ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች እጥረት እያጋጠመና እነዚሁኑ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚደረጉ ትግሎች እየበዙና ከጊዜ ወደጊዜም እየጠነከሩ መምጣት፣ የአደላደል መዛባትም እየተፈጠረ፣ ሽሚያ ውድድርና ፉክክርም እንዲሁም አለመግባባቶች እየተበራከቱ ሲመጡ፤ የሕዝብም አስተሳሰብና አመለካከት ውሎ አድሮ እየሠፋ፣ እያደገና እየተለወጠም እንደመጣ እንረዳለን።

በአጠቃለይ ከሰው ልጅ የብዙ-ጎንዮሽ ዕድገትና ለውጥ ጋር የተለያዩት የሰው ልጅ ህይወት ዘርፎች በአንድ መንደር፣ ከተማ፣ ክፍለ-ሀገር ወይም በሀገር ደረጃ በወጉ ለማስቀጠል ህግና ደንብ አውጥቶ፣ ህጎችንም በየጊዜው እያሻሻለ፣ እነሱን ለማስፈጸም የሚችል፣ ያንን መመሪያ የሚደረገውን ሕግም እንዳይጣስ የሚከታተል፣ አብሮ የመኖርንና በጋራ ህግም የመተዳደርን



ሃይል ሊያከናውናቸው ያልቻላቸውን ግዙፍ ተገባሮች ለማከናወን አቅምና ጉልበትን ያገኛል። ኢሕአፓ ሁኔታዎቹ ሲለወጡ፣ ድርጅቱም ሲሰፋና ሲያድግ፣ ውስጣዊ ሁኔታዎቹ ግድ የሚሏቸው ለውጦችን ማድረግ ይጠበቅበታል።

በሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ርዕዮተ-ዓለም ላይ የሚመራ ፍትሃዊ ሥርዓት እስከሚመሠረት ድረስ በማንኛውም ሀገርና ኅብረተሰብ በዉስጥ፣ ኢትዮጵያንም ጨምሮ፣ ሊገለሉ፣ ሊበደሉና ሊጨቆኑ የሚችሉ ብሔረሰቦች፣ ዉሁዳን ወይም አናሳ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የቡድን መብትን ጥያቄ በደፈናው ሥፍራ ማሳጣት ይገባል ወይም አስፈላጊ አይደለም ማለት ስህተት ይሆናል። ትክክለኛ የሚሆነው በደል በተፈጠረበት ጎራ ሁሉ ፍትህ እንዲኖር መታገሉ ብቻ አማራጭ-የለሽ የትግላችን ኢላማ ይሆናል ማለት ነው። የቡድን ነጻነት ከግለሰብ ነፃነት ጋር ጎን ለጎን ሊኖሩ አይችሉም የሚሉ ቢኖሩም፣ አንዳንዶቹም ከዚህ አልፈው የግለሰብ ነጻነት እስከተከበረ ድረስ ቡድንም የግለሰብ ስብስብ ነውና ነጻነቱ በተዘዋዋሪ “ስለተከበረ” ለምን ይህን በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል የሚል ተቃውሞ ቢያሰሙም፣ ማንኛውም ኅብረተሰብ ዉስጥ የዘርም ሆነ የዕምነት ወይም ሌላ መድልዎ በአንድ በተወሰነ ክፍል ላይ የሚፈጸም በደልን የሚያስከትል ተግባር እስካለ ድረስ የግለሰብ ነጻነት ብቻውን የቡድንን መብት ይፈታል ማለት አይቻልም።

______________//_____________

የሃሳብ ልዩነቶች በድርጅቱ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፣ ልዩነቶችን በወጉ ካስተናገድናቸው ወደቅራኔ ከዚያም ወደመለያየት እንዳያመሩ ማድረግ ግን ሁሌም አስፈላጊ ነው። ልዩነቶች እስኪባባሱ መጠበቅ የለበትም። በድርጅቱና በሕዝቡ (ሌላውን ተቃዋሚም ጨምሮ) መካከል መከባበርና አንድነት እንዲኖር ለማድረግ ደግሞ የድርጅቱ አባላት (አመራሩን ጨምሮ) ከህዝብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጤናማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች አመለካከቶችን የሚገፉትንና እኛን አይመስሉም የምንላቸውን የተቃዋሚ ድርጅቶች ትምህርት በማይሰጥ መንገድ መተቸትም ሆነ መዝለፍ ቀዳሚ ጉዳቱ ለራሥ ነው። ይህ ማለት ግን በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ የምንቃወማቸው አመለካከቶች ካሉና ከተሠራጩ እነዚህ ላይ አስተያየት መሰጠት የለበትም ማለት አይደለም፣ ዝምታ ደግሞ ከተጠያቂነት አያድንም።

VI. <u>ኢሕአፓ አሁን ካለበት ሁኔታ ወጥቶ በርካቶችን ሶሽያል ዴሞክራቶች በማሰባሰብ ነው የሚጠብቀውን ግዙፍ</u> <u>ሃላፊነት ሊወጣ የሚችለው</u>

በሶሻል ዴሞክራሲ ርእዮት እየተመራ፣ ራሱም እያደገና እየተለወጠ የሚመጣው፣ የነገው ኢሕአፓ መንግሥትን ፍትኅ አመንጭና የእንክብካቤ-ሥርዓት መፍጠሪያ ሊያደርገው ይገባል፣ ይቻላልም። የሠራተኛውን፤ ባጠቃላይ የሠርቶ-አደሩን ሕዝብ፣ የውሁዳንን፤ የሴቶችን፤ የህፃናትን፣ የአካለ ስንኩላንን፤ የአዛውንቶችን ወ.ዘ.ተ መብት የሚያስከብሩ፤ የግለሰብን ነጻነትን የብዙሃኑን መብት እስካልጎዳ ድረስ የሚያዳብሩ፤ የኤኮኖሚ እድገትን የሚያበረታቱ፤ ለሁሉም ዜጋ የጤናና የትምህርት ዋስትና የሚሰጡና የተፈጥሮ ከባቢን/ Environment የሚንከባከቡና ከጥቃት የሚከላከሉ ፕሮግራሞችን እያወጡ ማስተዳደር ይሆናል ግቡ።

አሁን በኢሕአፓ አባላት ተቀባይነት ያገኘው በሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ርዕዮት መመሪያነት ሠፋ ያለ ሃይል ለማሰባሰብ የሚንደረደረው ሠነድ በሚያማትረው ሂደት አንድ ጠንካራ ሃይል ለመፍጠር ይቻላል የሚል ዕምነት አለን። በሶሽያል ዴሞክራሲ የሚመራ ጠንካራ ሃይል ከተፈጠረ ደግሞ ትግሉ አጠር ባለ ጊዜ ውስጥ በድል ሊጠናቀቅ ይችላል። ለወደፊቷ ኢትዮጵያ ከዚያ ለለውጥ ከተፋለመው ትውልድ አባላት መሀል በህይወት ካለው ዉስጥ ዕምነቱን እንደያዘ ያለውን ክፍል ለታሰበው ለውጥ ለማሠለፍ ከተቻለ ዛሬ ሀግራችን ዉስጥ ያለውን አስከፊም፤ ተስፋ ሰጪም፤ ሁኔታ ውስጥ አጠር ባለ ጊዜ ዉስጥ ለመለወጥ ይቻለናል። ኢሕአፓ እያደገና እየሠፋም ሲመጣ ባነስተኛ



ሶሻል ውል (ኮንትራት) የሚጥሱትንም በተመለከተ በወጉ የሚዳኝ አንድ ውስብስብ ተቋም አስፈለገ። ይህም ተቋም ከተለያዩ ሙከራዎችና የአደረጃጀት እርከኖች በኋላ በአሥራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን አካባቢ መንግሥት/ ስቴት የሚል ስያሜ አገኘ። ይህ ዳር-ድንበርና ሉዓላዊነት ያለው ዘመናዊ መንግሥት በአገራት ስምምነት ለመጀመሪያ ጊዜ በዌስትፋሊያ (ጀርመን) ውስጥ የተደረገና በሁሉም አገሮች ላይ አቅምና ተቀባይነት እያገኘ የመጣው የተደራጀና የራሱ ወታደር ያለው የመንግሥት አወቃቀር ስምምነት ነው።

ከሕዝብ ዕውቀት መዳበር፣ ከምርት መሳሪያዎችና የምርት እድገት፣ በተለይም ከኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ የሥራና የኑሮ ሁኔታ ለውጦች ጋር አዳዲስ ፍላጎቶች፣ አዳዲስ ግንኙቶችም እያደጉና የተለመዱት ነባር ሥርዓቶችም፣ ችግሮችን ሁሉንም መፍታት እየተሳናቸው መጡ። ለአብነት ያህል የግሪክ ፈላስፋዎች ታሪካዊ ዉሱንነት ያላቸው ቢሆኑም እንኳ በተወሰኑ ከተሞች (ሲቲ ስቴትስ) እነሱ ዜጎች ናቸው ያሏቸውን (ባሪያዎች የሚሏቸውን አግልለው) የሚያሳትፉ መሰተዳድሮችን መሠረቱ። የዴሞክራሲና የሕዝብ መንግሥት ርዕዮት-ዓለምንም አስተዋወቁ። የሀብትና የአቅም እንዲሁም የጥቅም ልዩነቶች እየተጠናከሩ ስለመጡ በዚያን ጊዜ የነበረው ይህ “መንግሥት” ተብዬ ተቋምም የጠንካራዎቹ መገልገያ መሆኑን ለመላው ሕዝብ ግልጥ እየሆነም መጣ።

በአንድ ሀገር ዉስጥ በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን ለሁሉም በሚስማማ መንገድ ሊፈታ የሚችል “ፍትሐዊ” መንግሥትም ማግኘት ሳይቻል ቀረ። ስለዚህም የተለያዩ የኅብረተብ ክፍሎች የየራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ሊገልጥ ይችላል የሚሉትን አማራጭ ሃሳብ በተደራጀ መንገድ ለመግለፅ ተገደዱ። ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ምሑራንም የወቅቱን ኢክኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተንተርሰው ጥናት በማድረግ የሚያምኑበትን የተጠናቀረ ሃሳብ አቀረቡ። የከበርቴዎችን የምርት ግንኙነት መሠረት በማድረግ “የሊበራል ዴሞክራሲ” በመባል የታወቀው ርዕዮት አቀንቃኞች፤ አዳም ስሚዝ መሠረት ጣዩ ነው፤ የገበያ-ኢኮኖሚና የከበርቴው ዴሞክራሲ አስፈላጊ፣ ጠቃሚ፣ ዘላለማዊም እንደሆኑ ይሰብኩም፤ ይወተውቱም ጀመር።

ስለኅብረተሰባዊ ለውጥ አስፈላጊነትና እንዴትም የፖለቲካ ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል ብዙ በመጻፍና በመስበክ ወደ አደባባዩ የወጡት እንደካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ ያሉ የሶሲዮሎጂ የፖለቲካ ሊቃውንትን ወደመድረኩ ብቅ ያደረጉ ማሕበራዊ ክስተቶች በተለይ ከአውሮፓው ኢንዱስትሪያል ሪቮሉሽን

በኋላ የተፈጠሩ ክስተቶች ናቸው። ባለሃብቶች በአጠቃላይ፣ የፋብሪካ ባለቤቶች ደግሞ በተለይ፣ ለእነሱ ጉልበታቸውን በመሸጥ የሚኖሩትን በከተሞች የተጠራቀሙ ሠራተኞች በዝቅተኛ ደሞዝ ብዙ ያሠሯዋቸው ስለነበረ፣ከላይ የተጠቀሱትና የነአዳም ስሚዝ ተቃራኒ የሆነ አመለካከት የነበራቸውና ከላይ ያነሳናቸው እንደ ማርክስ፣ ኤንገልስ፣.. ዓይነቶች፣ እያደረ "ማርክሳዊ" በመባል የሚታወቀውን፣ የላብአደሮችን በመጨረሻም የጠቅላላውን ሕዝብ ጥቅም ያራምዳል ብለው ያመኑበትን ይህንን የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም በቲኦሪ ደረጃ እየተነተኑ አስፋፉ፣ በወቅቱም ሆነ ሄየኛው ክፍለ-ዘመን ከገባ በኋላ በተለይም የሩሲያ የጥቅምት አብዮት ተከትሎ በዓለም-አቀፍ ደረጃ የብዙውን ሠራተኛና ምሁር ቀልብም መሳብ ቻሉ። በመጀመሪያ በዚሁ በማርክሲዝም ያምኑ ከነበሩት መሐከልም የተወሰኑት፣ ልክ እንደነማርክስ ለውጥ ፈላጊዎች ቢሆኑም እንኳ የነማርክስን አስተሳሰብ ሁለንተናዊነት(ዩኒቨርሳሊስም)እና ተግባራዊነት (ፕራክቲካሊቲ) ግን ቀስ-በቀስ በጥርጣሬ ማየት ጀመሩ። በእነዚህ ኤኮኖሚስቶችና የፖለቲካ አመለካከት አፍላቂዎች አመንጪነትም ነበር ዝቅ ብለን የምንገልጠው ለየት ያለው ርእዮተ-ዓለማዊ ዘርፍም ያቆጠቆጠው።

## III. <u>ሶሽያል-ዴሞክራሲያዊ ርዕዮተ-ዓለም ታሪካዊ አመጣጥና ዋና ዋና መገለጫዎቹ</u>

ሶሽያል ዴሞክራሲ እንደ አንድ አማራጭ የለውጥ መመሪያ ሊሆን የሚችል ርእዮት፤ ሆኖ መታየትና ስር መስደድም የጀመረው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ በተለይም በጀርመን፤ በጣሊያንና በፈረንሣይ ዉስጥ ነበር። በስተኋላ የራሱን ባህሪያት እያገኘ ይምጣ እንጂ ዋነኛ ምንጩ በመደብ ቅራኔ ላይ ተመሥርቶ የተነሳውና ከ 1850 እስከ 1870 ድረስ በአውሮፓ ዉስጥ እየተስፋፍም የመጣው የሶሽያሊስት "ርዕዮት/አይዲኦሎጂ" ወይም "ማርክሲዝም" ነው። በየሀገሮቹ ዉስጥ የካፒታሊስቶቹን ምዝበራና ግፍ፣ በዓለም ደረጃ ደግሞ የአፍቅሮተ=ንዋይ ትኩረታቸውንና የርስ-በርስም ሽሚያቸውን፣ እነዚህ ባህሪያት ደግሞ የሚያመጧቸውን ወረራዎችና ጦርነቶች ለመደበቅም ሆነ ለመካድ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጠረ። እንደ ማርክስ ያሉት ዓብዮታዊ ምሁራን የካፒታሊዝምን ውስጣዊ ብልት አንድ ባንድ አብጠርጥረው በማሳየት ከበርቴዎቹ በማምረቻ መሣሪያዎች ባለንብረትነታቸው ላይ ተመስርተው በደሞዝ የሚያሠሯቸውን ሠራተኞች ከመጠን በላይ እንደሚበዘብዟቸው ለማሳየት ቻሉ። ከዚያም በላይ ካፒታሊዝም ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በነፃ ወይም በርካሽ ለማግኘትና የኢንዱስትሪ



ነገር ግን ለሊበራል ዴሞክራሲ የቆሙት ርዕዮቱን በዚህም ምክንያት ይነቅፋሉ፣ ለሀብታሞቹ ጥብቅና በመቆም የቀረጥን መብዛት ይቃወማሉ። ከእነሱም በባሰ መልክ ደግሞ፣ ዓይን-ባወጣና መረን-በለቀቀ ስግብግብነትና ግለኛነት ላይ የተመሠረተው "ኒዎ-ሊበራሊዝም" የተሰኘውን የካፒታሊዝም አስከፊ ገፅታውን የሚያራምዱት ደግሞ ሶሽያል ደሞክራቶችን ልክ ቀድሞ ኮሙኒስቶችን በሚያወግዙበት ደረጃ ነው ሲያወግዙ የሚሰሙት። የማርጋሬት ታቸርና የሬገን ዓይነቶቹ ስለሆኑ ከእነሱ ሌላ የተሻለ ነገር መጠበቅ የዋህነት ሊሆንም ይችላል።

ኢሕአፓ ሶሻል ዴሞክራሲ መመሪያ ርዕዮቴ ነው ሲል የትግሉ ራዕይ ምን መምሰል ይኖርበታል፤ የፖለቲካ ፕሮግራሙ፤ የሥነ-ምግባር መመሪያው፤ የውስጥና (በአመራር፤ በመዋቅሮችና በአባላት መካከል) እንዲሁም የውጭ (ከሌሎች ተቃዋሚዎች፤ ከህዝቡ፤ ከውጭ ሃይሎች) ግንኙነቱና የልዩነቶች አፈታት ዘዴዎቹ ምን መምሰል ይኖርባቸዋል የሚለውን ባጭሩ ለማመላከት ነው። አንድ የኢሕአፓ ዓይነት ፓርቲ በየጊዜው የሚታገልበትን ሀገራዊ ሁኔታ፣ የአካባቢና የወቅቱን የዓለምም ሁኔታ በማገናዘብ፣ አስፈላጊ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ መሰናዶዎችንም እያደረገ፣ የቆመላቸው የኅብረተሰቡ ክፍሎች ብሶቶችን፣ ችግሮችን፣ ግንዛቤዎችን፣ ለፍልሚያም ያላቸውን የመንፈስና ቁሳዊ ዝግጅቶችን፣ እያጠና በተግባር ሊያውላቸው የሚችላቸውን ፖሊሲዎች ያወጣል፣ ርምጃዎችንም ይወስዳል። በየወቅቱ ተገቢ የሆኑ ርምጃዎችን ከወሰደ ከበርካታ ችግሮች ከመዳንም አልፎ በኢትዮጵያም ዉስጥ ለሶሽያል ዴሞክራቲክ ሥርዓት መፈጠር ሁኔታዎችን በብርቱ ያመቻቻል።

ወደፊት ኢትዮጵያ ዉስጥ ሊፈጠር ስለሚገባው የፌደራል ሥርዓት አባላት ግልጽነት እንዲኖራቸው ቀጣይ ጥልቀት ያላቸው ጥናቶች ያስፈልጋሉ። በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ የተለያዩ ተሞክሮዎች ስላሉ እነዚያን የሌሎችን በማመሳከሪያነት አይቶ ስለጥቅምና ጉዳታቸው ተጨባጭ እውቀት ሊኖረን ይገባል። በፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ትስስር ላይ ያተኮረ የፌደራል መንግሥትና ሥርዓት አወቃቀር ለሃገሪቱ ሊያመጣ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ማሕበራዊ ፍትህ ሳይሰለቹ ማስተማር፤ ኅጠኝነትና ኅሣዊ ፌደራላዊነት በአገሪቱና በአብሮነት አመለካከት ላይ ያደረሱትን አደጋ አብሮ ማስተማር፤ በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ያለውንና ባመዛኙም ታሪካዊ የአገር ግምባታ ውጤት አንድነትን ለማጠንከር ብቻ ሳይሆን ልዩነቶችንም ለመፍታት ያለውን እቅድና ፍላጎት በግልጽ ማሳወቅ፤ መለያየት የሚያደርሰውን አደጋም አብሮ ማስተማር የግድ ይላል፤ ቅድሚያ የምንሰጠውም ሃገራዊ ጉዳይ ነው።

ርዕዮተ’ዓለምን መመሪያው ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ለመጀመሪያ ጊዜ የሀገሩን ያፖለቲካ ሥልጣን ይዞ በተግባር በታየበት በጀርመንና በኋላም “በኖርዲክ ወይንም ስካንዴኔቪያን ሀገሮች” የነበሩትንና ያሉትንም ሁኔታዎች መመልከት ይቻላል። ሶሽያል ደሞክራሲያዊ ድርጅቶች ለረጃጅም ጊዜዎች በህዝባቸው እየተመረጡ በሥልጣን ላይ በቆዩባቸው፣ አሁንም ያላቸው የፖለቲካ ተቀባይነት ጉልህ በሆነባቸው በእነዚሁ ሀገሮች ዉስጥ ከሕዝቡና ከኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ወርሃዊም ሆነ ዓመታዊ ገቢ ዉስጥ ከፍተኛ ቀረጥ ይሰበሰባል። በየሀገሮቹ ዉስጥ ያሉት ከበርቴዎች የቀረጡን መብዛት እየጠቀሱ ሶሽያል ዴሞክራቶችን ይተቻሉ፤ ለማጥላላትም ይሞክራሉ። ከተጠቀሱት ሆኖም ሕዝቡ በቀረጥ መልክ የሚሰበስበው ገንዘብ ለምን እንደሚውል ስለሚያውቅ መልሶ መላልሶ እነዚያኑ ሶሽያል ዴሞክራቶችን ነው በብዛት የሚመርጠው።

አንዳንዶቹ ልቅ የሆነ የነፃ-ገበያ አራማጆች በካፒታሊስቶቹ ላይ ምንም ዓይነት ሕጋዊ ቁጥጥር አያስፈልግም ብለው ስለሚያምኑ፣ በማሕበራዊና ኤኮኖሚ ህይወት ውስጥ ከመጠን ያለፈ የመንግሥት ጣልቃ-ገብነት አለ ወይንም ያደርጋሉ እያሉ ሶሽያል ዴሞክራቶችን ይከስሳሉ።

ሶሽያል ደሞክራሲ ሊወደስበት የሚገባውን አንዳንድ ጎኑን፣ የሌላው ተጻራሪ ርዕዮት ጠበቃዎች ማጥላያ ሊያደርጉት ይሞክራሉ። ለምሳሌ “በጠንካራ የእኩልነት መርህ(Strong Egalitarianism)ላይ ማትኮሩ”ን እንደጎፀጽ ይቆጥሩበታል። “በዓለማቀፋዊነት Internationalism) መርህ ላይ ማትኮሩን”ም አይወዱለትም። ሀገራዊ ከለልተኛነትን የሚያወድሱ ስለሆኑ ከሌሎች ሀገሮች ጋር መተጋገዝንና መተባበርን እንዲወዱት አይጠበቁምና ያው ተግባሮቻቸው የርዕዮተ-ዓለማዊ ትግሉ ገፅታዎች መሆናቸውን ተረድቶ እንደአመቺነቱ ምላሽ መስጠትን ይፈልጋሉ።

ሌላው ከዚህ ተያይዞ መገለጽ ያለበት እውነታ ቢኖር የገቢ ታክስን (income tax) በተመለከተ ያለው ሁኔታ ነው። በዴንማርክም ሆነ በስዊድን ከፍተኛ የሆነና እስከ 50% ሊደርስ የሚችል የገቢ ታክስ እንዳለ የታወቀ ነው። አብዛኛው ሕዝብ ግን የመንግሥት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ስለሆነ ይህንንም አውቆና አምኖበት ስለሆነ ደጋግሞ ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲዎችን የሚመርጣቸው፣ በታክስ መብዛትም ብዙ የሚያማርርበት ጉዳይ አይደለም። የተወሰኑ ግለኞችና ስግብግቦች የሉም ማለት ግን አይደለም። የታክስ መብዛትን መሠረት ያደረገ ተቃውሞና ሕዝባዊ እንቅስቃሴም ተፈጥሮ አያውቅም ማለትም አይደለም።



ወጤቶችንም ለመሸጥ ገበያ እንዲሆኑት የሶስተኛ ዓለም ሀገሮችን እየወረረ በቅኝ ግዛትነት ወደመያዝና ወደመቆጣጠርም እንደሚገፋ በበቂ ለማሳየት ቻሉ። የካፒታሊዝም ሥርዓትና ሊበራል ዴሞክራሲ የሚባለው የከበርቴዎችን ሥርዓት የሚገልጽና የሚያወድስ ርዕዮተዓለም ከዚያ በኋላ ትልቅ ፈተና ገጠመው። የ1929 ዓ/ም የዓለም ኤኮኖሚ ቀውስና እሱን ተከትሎ የመጣው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የካፒታሊስቱን ዓለም ትክክለኛ ባህሪያት አጉልተው ለማሳየት ቻሉ። ቀስ በቀስ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች በየሀገሩ መደራጀትና የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ፣ ደሞዛቸው እንዲጨመር፣ የሥራ ሰዓቶች እንዲያጥሩላቸው፣ የመደራጀት መብታቸው እንዲከበር መጠየቅና መታገልም ጀመሩ።

ካርል ማርክስና ፍሪዴሪክ ኤንግልስ የኮሚኒስት ማኒፌስቶ በመባል የሚታወቀውን በግልፅ ሠራተኛውን ለ’ዓመፅ የሚጠራ መግለጫ ያወጡት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ 1848 ነበር። ሆኖም ማርክስ እንደተነበየው ባደጉት የካፒታሊስት ሀገሮች ዉስጥ ላባደሮች ቀልጥፈው አብዮት ማድረግ አልቻሉም። እንዲያውም የመጀመሪያ “ሶሽያሊስት አብዮት” የተባለው በኢንዱስትሪ ባደጉት ሀገሮች ዉስጥ ሳይሆን በነገሥታት ተቀይዶ በቆየችና ገና በኢንዱስሪ ባልዳበረችው በሩሲያ ዉስጥ በነሌኒን የሚመራው አብዮት ሆነ። ከሩሲያው የ1917 ዓብዮት በኋላ ዓለም እንደ መንግሥታዊ ሥርዓት በተዘረጉ፣ በሶሻሊስትና ካፒታሊስት ርዕዮት አቀንቃኞች ለሁለት ተከፈለች። ነባሩን የካፒታሊስቶች ካምፕ የሚቃወምና በፖለቲካ ተወዳዳሪነትም የተሻልኩ ነኝ ብሎ የቀረበ ሌላ ካምፕ፣ የሶሽያሊስት ካምፕ የተሰኘ ተፈጠረ። *ከሁለቱም ካምፖች ጋር ሙሉ ለሙሉ መወገን ባልፈለጉና ስካንዴኔቪያን እየተባሉ በሚጠሩ አገሮች ውስጥ ሠፊ ሕዝባዊና መንግሥታዊ መሠረት የጣሉ በሶሽያል ዴሞክራሲ የሚመሩ የፖለቲካ ሃይሎች ተጠናክረው የመንግሥት ሥልጣን በሠላማዊ መንገድ በምርጫ በመያዝ ለሶሽያል ዴሞክራሲ አመለካከት ተጨባጭነትና ሊሠራም እንደሚችል አመላካች ሆኑ።*

በዳበሩትና በወቅቱ በመላው ዓለም ላይ በመንሠራፋት ላይ የነበሩትን ትልልቆቹን ሀገሮች የናጠ ታላቅ የኤኮኖሚ ቀውስ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1929 መፈጠር ባመዛኙ ነጻ የገበያ ሥርዓት ነው የተባለለትን የካፒታሊዝም የገበያ ሥርዓት ለውድቀት የሚያበቁ ዓይነታዊና ውስጣዊ ተቃርኖዎች እንዳሉት ያሳየ ስለነበር፤ ከዚያ ጠቃሚ ግንዛቤዎች ተገኙ/ተወሰዱ። ከዚህ ቀውስ ትምህርትን በመገብየት መንግሥታትን የየኢኮኖሚያቸው ተቆጣጣሪ የሚያደርግና ይህንን፣ የነአዳም ስሚዝንና ዴቪድ ሪካርዶን ክላሲካል ኤኮኖሚክ ቲዎሪና እንዲሁም

የወግ-አጥባቂው ፖለቲካ (የኮንሰርቫቲዝም) አባት የተባለውን የኤድመንድ በርክን የወግ-አጥባቂ ርዕዮት ለጊዜውም ቢሆን የሻረና የሶሻል ዴሞክራሲን መሠረታዊ አመለካከት ያካተተ ኤኮኖሚክ ቲዎሪ ማውጣትን ግድ ያለ ሁኔታ ተፈጠረ። በኢኮኖሚው ዘርፍ ተመራማሪ ከነበሩት መሀል እንግሊዛዊው ኤኮኖሚስት ጆን ሜይናርድ ኬይን ወቅቱ ያጋለጣቸውን የካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ችግሮች ለመፍታት የሚንደረደር የኢኮኖሚ ንድፈ-ሃሳብ (ቲኦሪ) አቀረበ። ይህም ባመዛኙ ከሶሻሊዝምም፤ ከካፒታሊዝምም ጠቃሚ ጎኖች ተውጣጥቶ የተጻፈው የምጣኔ ሃብት አወቃቀር፤ አያያዝና አስተዳደር ቲዎሪ በብዙዎችም ዘንድ ተቀባይነትን እያገኘ መጣ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ "ዜጎቻቸውን ተንከባካቢ ሀገሮች/ዌልፌር ስቴትስ እየተባሉ በሚጠሩ በርካታ አገሮች ውስጥ እስከ 1980ዎቹ አጋማሽና መጨረሻ ጊዜ ድረስ ለበርካታ ዓመቶች የጆን ሜይናርድ ኬይን ኢኮኖሚያዊ ቲኦሪ በመመሪያነት ለማገልገልም በቅቶ ሲሠራበት ቆይቷል። የማርጋሬት ታቸርና የሮናልድ ሬገን "ኒዎ-ሊብራል" ቲዎሪ እንደገና በምዕራቡ ዓለምና በሚቆጣጠሯቸው የዓለም ክፍሎች ዉስጥ ለማቆጥቆጥና ለመንሠራፋትም ችሎ በበርካታ ሀገሮች ዉስጥ ሠራተኛው መደብ፣ ሠፊው ሠርቶ-አደር ህዝብና ህዳጣን የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ እንዲሁም ሴቶች፣ በመጠኑም ቢሆን ከ1970ዎቹ እስከ 1980ዎቹ ድረስ፣ ተቀዳጅተው የነበረ መብታቸውን መልሰው እስከመገፈፍ ደረሱ።

እነዚህ የኒኦ-ሊበራል ኢኮኖሚክ ቲዎሪ አራማጆች ቀሪውን ዓለም ለራሳቸው ምዝበራ በሚያመች መንገድ እንዲጓዝ በማድረግ ከዘላቂ የዕድገት ጎዳናዎች ለማደናቀፍ ጥረዋል። ከ1960ዎቹ እስከ 1980ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በካፒታሊስቱ የኤኮኖሚውና ፖለቲካው መዋቅራዊ መስተካከል መርሐ-ግብርና የልማት ቲዎሪ (Structural Adjustment Program - SAP & Development Theory) መሠረት ኢኮኖሚያቸውንና የፖለቲካውን አካል ሚና እንዲያስተካክሉ በዓለም የንግድ ድርጅት (WTO ወይም GATT ይባል የነበረው)፤ በዓለም ባንክ (World Bank) እና በዓለም-አቀፍ የገንዘብ አበዳሪ ተቋም (IMF) አማካይነት ጫና ተደርጎባቸው የቆዩት የላቲን አሜሪካ አገሮች ቢያንስ እነዚሁ አገሮች እንዲጓዙበት የተተወላቸው ጠባብ መንገድ እንደፈለጉትና እንደጠበቁት እድገትን ሳይሆን ኪሣራን፤ የእንጡራ ሀብት ዕድገትን ሳይሆን በካፒታሊስቱ አገሮች ላሉ ባንኮች ባለ ዕዳነትን፤ ወ.ዘ.ተ. ነበር ያመጣባቸው። ከነዚሁ አገሮች ውስጥ አብዛኞቹ በብዙ ተጋድሎ ከተጫነባቸው የኒኦ-ሊበራል ቁጥጥርና ወጥመድ እየተላቀቁ፣ በራስ የመተማመንና ባመዛኙም ወደ ሶሻሊዝም ባጋደለ የሶሻል ዴሞክራሲ አመለካከት



የኢኮኖሚ፣ የማኅበረሰባዊ ፖሊሲዎችን ሲነድፍም መመሪያውና ማነጻጸሪያው አድርጎ፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታም የሚሠራበትን መንገድ አስተካክሎ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ የወደፊት ሕይወት አዲስ፣ የተሻሻለ፣ በቀጣይነት የሚያድግ፣ የሕዝቡን ነፃነት ከማኅበራዊ ፍትሖ ጋር አጣምሮ የሚጓዝ ሊያደርገው ይገባል። የፕሮግራሙን አቀራረጽ በየጊዜው እየመረመረ፤ የድርጅቱን ህግና ደንብ ከድርጅቱ እድገትና ጥንካሬ፣ ድርጅቱ አሁን በተፈጠረው አጋጣሚ ከሕገ-ወጥነት ማዕቀብና ከህቡዓዊነት ግርዶሽ ተላቆ በሕጋዊነት በይፋ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር እያገናዘበ በማሻሻል፣ የአባላቱንም የሥነ-ምግባር መመሪያ እንደዚሁ ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙና አባላቱ ሁሌም አንፀባራቂ ብቁነትን ለማግኘት እንዲችሉ በማድረግ ይሠራል፤ ሊሠራ ይገባዋልም።

የግለሰቦችም መብትና ግዴታ ቢሆን የሚቀረጸው መንግሥት በሚመሠረትበት ሂደትና ስምምነት ወይንም ውል (በሶሻል ኮንትራት) መሠረት ስለሆነ፣ ተቆጣጣሪነትና አስፈጻሚነት አብረውት በሚኖሩት የህብረተሰቡ አባላት ስምምነትና ህብረተሰቡም በሚፈጥረው የአመለካከት፤ የብቃት፣ የችሎታ እንዲሁም የተቋሞች ግንባታ ክልል ውስጥ ነው። ይህም ማለት በስመ-የግለሰብ ነጻነት ሕብረተሰቡ መመሪያዬ ብሎ ካወጣው ሕግ በላይ መሆን አይቻልም፤ በለውጡም ህብረተሰቡ ወይም መንግሥት ባፈተተው የግለሰብን ነጻነት መጋፋት አይችልም፤ መብትም የለውም። እነዚህም ሊገፈፉ የማይችሉና አሉታዊ/ ኔጋቲቭ የሚባሉ የግለሰብ መብቶችን (ለምሣሌ፤ በባርነት አለመገዛት፤ ከማናቸውም ዜጋ ተለይቶ ለጥቃትና ለመድልዎ አለመመቻቸት፤ ሃሳብን በነጻ መግለጽ፤ ከፈለጉት ጋር መደራጀት፤ መሰብሰብ፤ ወ.ዘ.ተ፤) ማንም አካል፤ መንግሥትም ሆነ ሌላ ስብስብ ወይም ግለሰብ ወይም ሕብረተሰብ ሊነፍግ የሚያስችል መብት የለውም።

እንግዲህ የግለሰብ መብት በዚህ መልኩ ነው ይከበራል፤ መከበርም ይኖርበታል የሚባለው። የእኩልነትና የፍትህ ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ ከግለሰብ መብት በተጨማሪ አንድን ቀደም ብሎ በደል/ጉዳት የደረሰበትን ዜጋ ለይቶ ሊመለከትበት የሚገባ መመዘኛ ወይንም መስፈርት የፖለቲካ ምህዳሩ ሊኖረው ይገባል። ይህም በዚያ ዞግ ከደረሱበት ልዩ ሁኔታዎች ለማውጣት፣ ፈረንጆቹ እንደሚሉት "Affirmative Action" (ጤናማና ፍትህ አምጪ ፖሊሲ) በታሪክም ሆነ በወቅቱ የተነጠሉ/የተጎዱ ክፍሎችን ለይቶ ፍትህ የሚሰጥበት መብት መሆኑ ነው።

የሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮት ዋና ዋና አመለካከቶችና የሚሠነዘሩበት ትችቶችን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት ይጠቅማል። የሶሻል ዴሞክራሲ

አሮጊቶች እንዲሁም አካለ-ስንኩላን በቂ ጡረታና እንክብካቤ እንዲያገኙ፣ ሥራ-አጦች ተመልሰው ሥራ እስከሚያገኙ ድረስ ለመኖር የሚያስችል ርዳታ እንዲያገኙ፣ ሕፃናት ሙሉ እንክብካቤ እንዲያገኙ፣ እመጫቶች በቂ የዕረፍት ጊዜ ከሙሉ ክፍያ ጋር እንዲያገኙ፣ ለማድረግ ነው። የትልቅ ራዕይ አካል የሆነ መርህ፣ ጠንካራ ትግል ማድረግንና ረጅም ጉዞንም የሚጠይቅ ዓላማ፣ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ማንኛውንም ዋጋ መክፈል የማይበዛበት ክቡርና ንውድ ጉዳይ ነው።

8. ሶሽያል ዴሞክራሲ ከመሠረታዊ መርሆዎቹ አንዱ፣ በአንድ ሀገር ዉስጥም ሆነ በዓለም ደረጃ በሰው-ሠራሽ ምክንያቶችም ሆነ በሌላ ከተጎዱትና በደል ከደረሰባቸው ጋር መተባበርና መረዳዳት አስፈላጊና ተገቢም ነው ብሎ በማመን፣ ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ትብብር በማድረግ፣ ድጋፍን በመግለጽ፤ የመልካም ጉርብትና ፖሊሲን በመከተል፤ ጤናማና አቅም በፈቀደው ልክ ርዳታን ለሚፈልጉ ሁሉ አቅም እንደፈቀደ የመለገስ የውጭ ፖሊሲን መከተልን የግድ ይላል።
9. ሶሽያል ዴሞክራቶች ለጭቁኑና ለተበደለው የኅብረተሰብ ክፍል ወገናዊነትን ቢያሳዩም በመላው የሀገሪቱ ሕዝብ ዘንድ ደግሞ የሁሉንም መብት፣ እኩልነት፣ ለማስገኘት ስለሚጥሩ ከበሬታና ተአማኒነትን ሊያገኙ ይገባል። ሶሽያል ዴሞክራቶች የሰፊው ሕዝብ ተጠሪዎች ናቸውና እንደከበርቴዎች ለግል ጥቅም አይስገበገቡም። በሥነምግባራቸው ከሌሎቹ በተሻለ ደረጃ ላይ ሊገኙ ነው የሚገባቸው። የህዝብን አመኔታ ሊያገኙ የሚችሉት ከሥነምግባር ብሉሹነትና ሙስና የፀዱ ሲሆኑ ብቻ ነው። ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ በተለይም የፖለቲካ ሥልጣን በሚጨብጡበት ሁኔታ ከፍተኛ የተጠያቂነትና የግልጽነት መስፈርቶችን ሊያሟሉ ይገባል። እንደ ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ ያለ በኅቡዕ እየታገለ ያለ ፓርቲም ቢሆን ከዚያ ከህቡዓዊ ሥራው ጋር የሚዛመድ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የግልጽነትና የተጠያቂነት መመዘኛን አውጥቶ ያንን በተግባር ያውላል።

10. የሀገርን የተፈጥሮ ሀብት በታላቅ የኣላፊነት መንፈስ በመያዝና በመጠቀም ያልተበከለና ጤናማ አካባቢን፣ ሀገርን፣ ዓለምን ለመጪ ትውልዶች ለማስተላለፍ መቻል ከሶሽያል ዴሞክራቶች የሚጠበቅ ተግባር ነው።
ኢሕአፓ የዚያን ለአብዮታዊ ለውጥ የተፋለመ ትውልድ ትልቅ ራዕይ በሶሽያል ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም መልክ እንደገና ህያው አድርጎ፣ የፖለቲካዊ፣



ላይ ከፍተኛ እምነት በጣሉ የዕድገትና ልማት አማራጭ (Alternative Developent Theory) ኤኮኖሚስቶች መርህ መሠረት ካፒታዝምን በመቃወምና ሶሻሊዝምንም በመጠኑ በመተቸት ሶሻል ዴሞክራሲን በስፋት መቀበል ጀመሩ። በዚህም ሥራቸው የካፒታሊስቱን ዓለም የልማትና የዕድገት ቲዎሪም የመተባበር/የመደጋገፍ (Interdependence) ሳይሆን የካፒታሊስቱን ዓለም “እጅ እያዩ ማደር ላይ” የሚጥል ወይም የተመጽዋችነት (Dependency Theory) ዕውነታን የሚፈጥር ነው ይላሉ። የዚህ አመለካከት አቀንቃኞች ትንታኔ የተመሠረተው በመዋቅራዊ (Structural) እና ታሪካዊ (Historical) ዕውነታዎች ላይ በመመሥረት ሆኖ’፣ በአሜሪካ ውስጥ በዘመኑ ጽሁፎቻቸው ገንነው ከሚነገርላቸውና የመንግሥትም ፖሊሲ እስከመሆን የደረሱላቸውን እንደ ታልኮት ፓርሰን (Talcott Parsons) የመሣሰሉትን ስትራክቸራል ሶሲዎሎጂስቶች ትንታኔ ፊት ለፊት በሚቀናቀን መልኩ እንደሚከተለው ይላሉ።

የካፒታል ክምችትና ዕድገት በራሱ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥና በራሱም ግብአቶችና ምርታማነት ላይ ብቻ ተመሥርቶ እስካልተንቀሣቀሰ ድረስ ይህ ዓይነቱ ሥርዓት ከውጭ የኤኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ነጻ ነው ማለት አይቻልም። “ግሎባላይዜሽንን አንተርሶ የዓለም ኤኮኖሚ የተያያዘ/የተደጋገፈ (Interdependent) ነው፤ አገሮች የተለያየ ተወዳዳሪ ጥቅም (Comparative Advantage) አላቸውና ከዚህ ዓይነቱ ኤኮኖሚ ሁሉም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ የሚለውን አስተሳሰብም አጥብቀው ይተቻሉ። የዚህ ዓይነቱን፣ የዴቪድ ሪካርዶ ኤኮኖሚክ ቲዎሪ ተተንተርሰው የሚያስተምሩትን ቀመር በማስተባበል “የዓለም ኤኮኖሚ እነርሱ እንደሚሉት የተያያዘ/የተዛመደ ቢሆንም (አንዳንድ አገሮች ባልሠለጠነ ሥራ Unskilled Labor) የተመረተ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት እንደመፈለጋቸው ሁሉ፤ ሌሎች አገሮች ደግሞ በርካሽ የሠራተኛ ጉልበት (Cheap Labor) የተመረቱ የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን፤ የፋብሪካዎችና ባጠቃላይም የካፒታል እቃዎችና ምርቶች ያስፈልጋቸዋል)፤ ስለሆነም እንደተባለለት ግንኙነቱ ግን በእቻነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። “እንዲያውም ብዙ አገሮች በሀብታም አገሮች ላሉ አበዳሪዎች ባለ እዳ ሲሆኑ፤ በነዚህ ሀብታም አገሮች ያሉ ባንኮች ደግሞ አበዳሪ ይሆናሉ። ብድሩ የሚከፈልበትን የብድር ዋጋ/አራጣ (Interest Rate) እና የአከፋፈሉን ሁኔታ የሚወስኑትም እነዚሁ አበዳሪዎቹ ናቸው። በዚህም መልክ ፍትሃዊ ያልሆነ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ግንኙነት ነው የሚፈጠረው። ስለዚህም የኒ’ኦ ሊበራል ኢኮኖሚ ቲኦሪ አቀንቃኞችና ተጠቃሚዎችም

ለማሣመን እንደሚሞክሩት ሁሉንም የሚጠቅምና መደጋገፍም ጉልህ ገጽታው ሳይሆን፣ እያራመዱት ያለው "የግሎባሊዜሽን" ንድፈ=ሃሳብና መረብ ከሚባለው የራቀና አንዱን ወገን የሚጠቅም መሆኑን በማሳየት፣ ዓለማችንን የተሻለ ሥፍራ ለማድረግ ዕውነተኛ መደጋገፍ ግን አስፈላጊ ስለሆነ ከፍ ብሎ ከተገለጸው ዓይነት የተዛባ የኤኮኖሚ ግንኙነት የጸዳ የመደጋገፉ ጽንሰ-ሃሰብን ለማግኘት ሌላ ምንጭ በማስፈለጉ በአማራጭነትም F. Cardoso እና E. Faletto የሚባሉት የምጣኔ ሃብትና የዕድገት ንድፈ-ሃሳብ ጸሐፊዎቹ ወደሚሰጡት ጥልቀት ያለው ትንታኔ ይዞራሉ።

በካርል ማርክስም ሆነ እሱን ተከትለው በመጡ የፖለቲካ ተመራማሪዎችና ጸሐፊዎች አመለካከት ሶሻሊዝም በላብአደሩ አምባገነንትና በአንድ የሠራተኛው ፓርቲ ራዕይ ላይ ተመርኩዞና የካፒታሊስቱን የኤኮኖሚ፤ የፖለቲካና ማሕበራዊ ቅኝቶች ደምስሶ "ሁሉም እንደየፍላጎቱ" (according to his/her needs) የሚኖርበትን ኮሙኒዝምን የሚገነባ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ሥርዓት እንጂ ከላይ በሶሻሊስት ኢንተርናሽናል ማኒፌስቶ ውስጥ እንደተገለጸው በነጻነት፤ እኩልነት፤ ወንድማማችነት/እህትማማችነት፤ በማሕበራዊ ፍትህ መተከሎችና በተለይም ደግሞ በካፒታሊስቱ የገበያ ሥርዓት ተደግፎና በውክልና ዴሞክራሲም የሚተዳደርና የብዙ ፓርቲዎችን የመኖር ህልውና የሚቀበል ሥርዓት ሆኖ እንዴት ወደዚያ፣ ሶሽያሊዝም ወደተባለው፣ ሊያደርስ ይቻላል የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አግባብ ይኖረዋል።

በሶሻል ዴሞክራሲ አመለካከት ማርክስ አጥብቆ የተከራከረለትና በበርካታ ጸሐፊዎችም ዘንድ ከተተቸበት ሥራዎቹ ውስጥ ዋነኛው በወሳኝነት ያስቀመጠው የኤኮኖሚው/የማምረቻ መሣሪያው ባለቤትነት ጉዳይ ሳይሆን የመንግሥትና ሕዝብ የፖለቲካ ሚና ነው እኩልነትንና ፍትህን ማምጣትና ማስከበር የሚችለው የሚለው መልእክቱ ነው። የሶሻሊዝም እንደ አማራጭነት አለማደግ፤ ብሎም በሶቭየት ኅብረት የሚመራው "ሶሽያሊስት ካምፕ" በመባል ይታወቅ የነበረው እንደ አንድ አማራጭ የዓለም ሥርዓት መቀጠል ተስኖት መፈረካከሱ፣ በየአባል ሀግሮቹም ዉስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የነበራቸውን "የማኅበራዊ ፍትኅ መርሆዎች" እንኳ ለማስቀጠል አለመቻል ሶሽያሊስት ርዕዮት-ዓለምን ከፍተኛ ቀውስ ላይ ጣለው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ደግሞ በኬንዚያን/Keynesian የክብካቤ ኢኮኖሚክስ(Welfare Economics)አመለካከት ተመሥርተው በአውሮጳና በሰሜን አሜሪካ የተፈጠሩት የእኩልነትንና ፍትህን መሠረት የገነቡ በርካታ አገሮችን እውነታና የሶሻሊስቱንም ካምፕ መፍረክረክ ስንመለከት፤ በርግጥም ሶሻል ዴሞክራሲ



6. ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች እኩል ናቸው፣ በሀብት፣ በጾታ፤ በብሔረሰብ፣ በባህል፣ በዕምነት፣ በፖለቲካ አመለካከት ጭምር፣ ወይንም በአካለ-ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ልዩነት አይደረግባቸውም። ይህንን መሠረታዊ ዕምነታችንን በመግለጽ ብቻ ልንወሰን አንችልም። ኢትዮጵያችን ዉስጥ የጭቆና ሰለባ የሆኑ ክፍሎች ስላሉ መሰናክሎቹ በሙሉ እንዲወገዱ፣ ሁሉንም ችግሮች እያጠናን ተስማሚ መፍትሄዎችን መፈለግ ይገባናል። ኢትዮጵያ ከ 80 በላይ ብሔረሰቦች ያሏት ሀገር ነች። አወዛጋቢ ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉትን ከብሔረሰብ ጥያቄ ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች እንኳን ለጊዜው ከመዘርዘር ብንቆጠብ፣ በሁሉም ሲረገጡና ሲበደሉ የኖሩ ዉሁዳን ኅብረተሰቦች እንዳሉ የማይካድ ነው። ያሉትን ችግሮች አብጠርጥሮ ማወቅ፣ ማመንና መቀበል፣ ትክክለኛ ነው ብለን የምናምንበትንም ጉዳይ ማስተማር ይገባናል። የሕዝቡን እኩልነት መብት መረጋገጥ ከሚቃወሙት ጋር ደግሞ በሠላማዊ መንገድ የሚደረግ ፖለቲካዊ ትግል ተገቢና አስፈላጊም ነው።
7. ባደጉት የምእራብ ሀገሮች ዉስጥ እንኳን ከካፒሊስቱ ሥርዓት በፊት በነበሩት ሥርዓቶችም ዉስጥ ሆነ በካፒታሊስቶቹ ሊበራል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ዉስጥ ማህበራዊ ፍትህ (Social Justice) አልነበረም። የማኅበራዊ ፍትኅን አስፈላጊነት ግን የተረዱ በርከት ያሉ አስተሳሰቦች፣ በአንዳንድ ሥፍራም እንቅስቃሴዎች ተፈጥረው ትግሎችም ተካሂደዋል። ጭቁንና ምዝብር የሆኑት የኅብረተብ ክፍሎች ቀደም ብሎ በማርክሲዝም፣ ለጥቆ ደግሞ በሶሽያል ዴሞክራሲ ጭምር የሚመሩ እንቅስቃሴዎችን በመመሥረት በሰው ልጆች ታሪካዊ ዕድገት ዉስጥ የግራውን ርዕዮቶች የማኅበራዊ ፍትኅ አዋላጆች ሊያደርጓቸው ቻሉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ደግሞ የከበርቴዎች ስርዓት እንኳን በወጉ ያላደገበት ሁኔታ ነው ያለው። ድህነትና ችግር የተንሰራፋበት ሁኔታ ስላለ የማኅበራዊ ፍትኅ ጥያቄ እጅጉን አንገብጋቢም ነው። በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ የሚኖረው፣ መጠለያ ያጣው፣ የትምህርት ዕድል የተነፈገው፣ የሥራ እድል በሰበብ አስባቡ የተነፈገው፣ በአጠቃላዩ ማኅበራዊ ፍትኅ የጠማው የሕዝባችን ክፍል በርካታ ነው። ጥያቄው ኢሕአፓ እንዴት ነው ሕዝቡን በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ሊደራጅና ሊያታግል፣ ለድልም ሊያበቃ የሚችለው ነው። በሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ርዕዮተ-ዓለም የሚመራው ኢሕአፖም የሚያልመው ዛሬ ደሀ የምትባለውን ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ልማት በማሳደግ ትምህርት በነፃ ለሁሉም ዕድሜው ለሚፈቅድለት ዜጋ እንዲሰጥ፤ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ በነፃ እንዲሠጥ፤ ሸማግሌዎችና

1. ለማግኘት ግን መሠናክል የሚሆኑትን ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ ታግሎና በህዝብም ድምጽ ከሥልጣን ማስወገድ ወይንም መለወጥ አስፈላጊም፤ ተገቢም ነው ብሎ ያምናል። የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን፣ ክብሩን፣ ነፃነቱንና ፍትህን ሳይቀዳጅ የሚፈልገውን ሠላም ሊያገኝ አይችልም፤ ስለዚህም እነዚህ መብቶቹ እንዲከበሩለት በግምባር ይታገላል።
2. 2. የኢትዮጵያ ህዝብ በርሃብ አለንጋ ከመገረፍ፣ ለአንዴም ለሁሌም መላቀቅ አለበት። ከድህነትና ከርሃብ ሕዝባችን ነፃ ካልሆነ፣ ከርዕዮትዓለማችን የሚመነጩት ፖሊሲዎቻችንና የተጨባጩ ሁኔታ ግንዛቤዎቻችን፣ ከፊሉ ወይንም ሁሉም ስህተት አላቸው ማለት ነውና የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁሉም በፊት ከርሃብ ነፃ ሊሆን ይገባዋል።
3. 3. የኢትዮጵያ ሠርቶአደሮች ልክ እንደ ሀብታሞቹና እንደገዥ መደብ አባላት ሁሉ በሰብአዊነታቸው ብቻ ክብር፣ መብት፣ ነፃነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ማመንና በይፋና ዘወትርም ማሳወቅ ያስፈልጋል፣ እንደግለሰቦችም፣ እንደህብረተሰብ ክፍልም የሚገባቸውን ነፃነትና ሰብዓዊ ክብር እንዳይቀዳጁ የሚቃወሙም ስላሉ፤ ከሠርቶ’አደሮች ጋር በመወገን መታገልም የግድ ነው።
4. 4. እንደ ኢሕአፓ ያለ ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር አለበት። ሀገሪቱ ዉስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች በመንከባከብና በመቆጠብም በማልማትና ኢንዱስትሪዎችንም በማስፋፋት ብኩንነትንና ሙስናን በማስወገድ፣ እድሜው ለሥራ የደረሰ ሁሉ ሥራ እንዲያገኝ ለማድረግ መቻል አለበት።
5. 5. ሶሽያል ዴሞክራሲ ሰርቶአደሩም ሕዝብ ጭምር የንብረት ባለቤት እንዲሆን ይፈቅዳል፣ ይፈልጋልም። የሚቃወመው ከፍተኛ ንብረትን በማካበት በዚያ ንብረቱ አማካይነት ሠርቶአደሮችን ከመጠን በላይ እንዳይበዘብዙ ነው። ይህንን ደግሞ በህግና በመመሪያዎች ነው የሚገታው እንጂ ከበርቴዎችንም ሠቶአደሮችን ሳይበድሉ በፋብሪካዎቻቸው ዉስጥና በሌሎች የሥራ ተቋሞች ዉስጥ ሰራተኞችን ቀጥረው እንዲያሠሩ፣ ማለትም የበለጠ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ፣ ይፈልጋል፤ ያበረታታልም። የንብረት ባለቤትነታቸውንም ያከብራል። ከገቢያቸው ግን ተገቢውን ቀረጥ ያስከፍላል። ኢሕአፓ አርሶአደሮች የሚያርሱትን መሬት በግል ንብረትነት እንዲይዙ ይሻል። በከተማ ኗሪዎችም የግል ቤቶችና ንብረቶች እንዲያፈሩ ያደርጋል፤ መብታቸውን ያስከብራል።



ብቸኛ አማራጭ ሆኖና ያለብርቱ ተፎካካሪም እንደቀረ ማየት እንችላለን። ይህም አማራጭ ባመዛኙ በስካንዴኔቪያንና ኖርዲክ አገሮች ውስጥ የተረጋጋና የበለጸገ ሥርዓትን ገንብቶና በብዙ መልኩም ርዕዮቱ የሚጠይቃቸውን የእኩልነትና የማሕበራዊ ፍትህ ጥያቄዎችን ባግባቡ እያሟላ ያለ የፖለቲካ ሥርዓት መሆኑም በግልጽ ይታያል።

የሶሻሊስቱ ካምፕም ቢሆን ውስጡ በነበረው የንድ-ፈሣብ (ቲዎሪ)እና ተግባር አለመጣጣም ቅራኔ፤ ሲንከባለል በቆየውና መፍትሔም ባልተበጀለት የብሔርተኝነት ችግርና በካፒታሊስቱም ዓለም ያልነጠፈ ግፊትና ሤራ ከፈራረሠ ከ1989 ዓ/ም በኋላ ደግሞ በአንድ ወቅት የሶሻሊስት አመለካከት የነበራቸውና በዓለም ዙሪያም ይገኙ የነበሩ ሶሻሊስትና ኮሙኒስት የፖለቲካ ድርጅቶች ባመዛኙ ወደ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲነት መቀየር ተገድደዋል። ባንድ ወቅት “ዜጎቻቸውን የሚንከባከቡ መንግሥታት” (Welfare States) ተብለው ይጠሩ የነበሩ አገሮችም፣ ባመዛኙ በዚህ ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ዙሪያ የመንግሥትና የኤኮኖሚ አወቃቀራቸውን ለማስተካከል ሲሞክሩ ነው የሚታዩት። ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ የነበረው የእንግሊዙ “ሌበር ፓርቲ” በሕዝብ በሚደረግ ግፊት ሁሉንም ከዚህ በፊት የተደረጉ ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን ለሕዝብ የማቅረብ ፖሊሲዎች እንዳይለውጥ ቢደረግም ከዘመነ ማርጋሬት ታቸር ጀምሮ ከቀኙ በሚደረግ ጫና እየተንሸራተተ ያንን ባህሪውን እየለወጠ በመምጣት ላይ መሆኑ ይታያል። ጀርመን በገናና መሪዋ በቢስማርክ አማካይነት አንድ ሆና ከተመሠረተችበት ወቅት አምስት ዓመት በኋላ፣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1875 ዓመት ምህረት የተመሠረተው የጀርመን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ መመሪያው አድርጎት የቆየው የሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮት፣ እንደ ቲኦሪ በሃሳብ ደረጃ ወደ ተለያዩ ሀገሮች ሲዛመት ቆይቶ፣ ረዘም ያለ ጊዜ ቢወስድም በኋላ ግን በእንቅስቃሴ መልክ ተጠናክሮ፣ በበርካታ አገሮች የመንግሥት ሥልጣንም እስከመያዝ የደረሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና ቅንጅቶች፣ መመሪያ ለመሆን ችሏል።

የዚህን የሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ርዕዮት የተሟላና ህልው ትርጓሜ፤ ርዕዮቱ ያቀፋቸውን ዋነኛ ጽንሰ-ሃሳቦች፤ በርዕዮቱ ላይ ለማጥላላትም ሆነ በአግባቡ የሚነሱትን ትችቶች፤ ከሊብራል ዴሞክራሲ ጋር የሚመሣሰልበትንና የሚለይበትን፣ በተለይም ደግሞ ከወግ አጥባቂው ክንፍ ኒኦ-ሊበራል ፖሊሲዎች ደግሞ የሚለይባቸውን አጠር አጠር አድርገን ለማየት እንሞክራለን። ሶሽያል ዴሞክራሲን አንዳንዶቹ (ለምሣሌ እንደ ጀርመናዊቷ ሮዛ ለግዘምበርግና እሷን የመሣሰሉ ሌሎች ጸሐፊዎች/ታጋዮች ዕምነት) ካርል ማርክስ ወዳለመለትና

ወደታገለለት ወደሶሻሊዝም/ኮሙኒዝም የሚደረገው ጉዞ አማራጭ መንገድ አድርገው ሲመለከቱት፤ ሌሎች ደግሞ የሚረዱት ከዚህ በተለየ መንገድ ነው። ከቃሉ/ሐረጉ አሰያየም በግልጽ ማየት እንደሚቻለውም ስያሜው ከሶሻሊዝም ዋና ዋና የፍትህና እኩልነት መርሆዎችና ከካፒታሊስቱ የሊብራል ዴሞክራሲ (አንጻራዊ የፖለቲካ ነፃነት) አመለካከቶች ተውጣጥቶ የተቀመረ አመለካከት ነው። ከሶሽያሊዝም ርዕዮት የማኅበራዊ ፍትኅንና የዕኩልነት እምብርት የሆኑ ፅንሰሃሳቦች በሰፊው አተረጓጎማቸው ይወስዳል። እነሱን ከፖለቲካ ነፃነት ጋር አጣምሮ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታም ይፈጥራል።

እስቲ ለመንደርደሪያ ያህል ከዚህ በታች ያለውን፣ ከ "ሶሽያሊስት ኢንተርናሽናል መርሆዎች ዕወጃ" (Declaration of Principles) የተወሰደውን እንመልከት"።

- First, freedom that includes not only individual liberties, but also freedom from discrimination and freedom from dependence on either the owners of the means of production or the holders of abusive political power, as well as the ability to determine ones own fate.
- Second, it also must have equality and social justice, not only before the law but also having economic and socio-cultural equality as well, that promotes equal opportunities for all including those with physical, mental, or social inequalities, and
- Finally, it must have solidarity that practices unity and a sense of compassion for the victims of injustice and inequality."

የሶሻል ዴሞክራሲ ታሪካዊ ትርጉሙንና የፖለቲካ ቀመሩን ስንመለከት፣ እንዲሁም አሁን በተለያዩ አገሮች በተለይም ስካንዴኒቪያን ወይም "ኖርዲክ" እየተባሉ በሚጠሩትና በሌሎችም ይህንኑ ርዕዮተ-ዓለማዊ ፈለግ በሚከተሉ አንዳንድ አገሮች በሚሠራበት መልኩ ያለውን በተግባር አተረጓጎም ስንመለከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አዎንታዊ ግንዛቤዎች ነው የምናገኘው።



ሁኔታ ጋር አገናዝቦ፣ ዛሬ በሀገራችን ዉስጥ ያለውንና ነገና ተነገ-ወዲያም ሊሆን የሚችለውን በማጥናትና አማትሮም በማየት በግብር ሊውሉ የሚችሉ መመሪያዎችን (ፖሊሲዎችን) ማውጣትና እነሱንም በየጊዜው እየመረመረ ማስተካከል አለበት። ኢሕአፓ የድርጅቱን ራዕይ፤ የፖለቲካ ፕሮግራሙን፤ ህገ-ደንቡን፤ የልዩነቶች/ቅራኔዎች አያያዝ ሥልቱን፣ የሚከተለውን የውጭ ግንኙነት መመሪያ፤ ሲያወጣ በተጨባጭ ሁኔታ ጥናት ላይ ተመሥርቶ፣ በአባላት ሙሉ ተሳትፎ፣ ከርዕዮቱ ጋርም በማገናዘብ ሊሆን ይገባል።

ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሶሻል ዴሞክራሲን ለማስፋፋትና በዚህም ላይ በተመሠረተ እንቅስቃሴና ትግል መሠረት ሕዝቡ በጣም የሚፈልገውን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት እንዲችል አባላቱ ርዕዮተ-ዓለሙን በንድፈ-ሃሳብ ደረጃና በሌሎች ሀገሮች ዉስጥ እንዴት ተደርጎ በተግባር እንደዋለም ተመክሯቸውን በማጥናትና ሁኔታዎችንም በማገናዘብ በእኛስ ሀገር የትኞቹን፣ እንዴትስ በተግባር ማዋል እንደሚቻል እንደድርጅት ማጥናትና መማርም፤ ጠቃሚውን ወስዶን በድርጊት መተግበርም ይገባናል። አባላቱ ርእዮተ-ዓለሙን የፖለቲካ ሥራቸው መመሪያ ሊያደርጉት ይገባል ስንል በቅድሚያ ራሳቸው በበቂ እንዲያውቁት ያሻል ማለታችን ነው። ከዚያም በቀጣይነት አዳዲስ ገጽታዎችን በማጥናትም እንደኢትዮጵያ ባሉት ሀገሮች ዉስጥ በምን መልክ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችል ሊያገናዝቡ ይገባቸዋል።

ርእዮተ-ዓለሙ ለመላው የሀገራችን ዜጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና ፍትህን ለማስገኘት የሚያልም ቢሆንም፣ ለሚበዘበዙትና ለሚጨቆኑት የኅብረተሰብ ክፍሎች እኩልነትን ለማምጣት የሚታገል፣ ስለዚህም ከምዝብርና ጭቁን *መደቦች ጋር ወገንተኛነት ያለው ርዕዮት ነው።* በግል ጥቅም ማራመድንና በግል ሃብት ማካበት ላይ ብቻ በሚያተኩሩ ስግብግብ ከበርቴዎችና የግፍና የበደል ሥርዓቶችን ከሚያራምዱትና የመንግሥትን ሥልጣን ከጨበጡ ሃይሎች ጋር ምንጊዜም በሠላማዊና ፖሊቲካዊ መንገድ ቢሆንም ጠንካራ የፖለቲካ ፍልሚያ ማድረግ የማይቀር መሆኑንም የተቀበለ ርዕዮትዓለም ነው። ስለሆነም የኢሕአፓ አባላት የፓርቲውን ርዕተዓለም ዋና-ዋና መርሆዎች ይዘትና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታም በየወቅቱ ሊኖረው የሚችለውን አተረጓጎም ለሠርቶ-አደሩ ሕዝብ ያለመታከት ከሕይወቱ ጋር አዛምደው ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል። የኢሕአፓ ርዕይተ-ዓለማዊ መመሪያ፣ ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ርዕዮተ-ዓለምም፣ የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች ሊያካትት ይገባዋል።

ኢ.ሕ.አ.ፓ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ይፈልጋል፣ ታዲያ ለይስሙልኝ በስመ ዴሞክራሲ በየጊዜው ምርጫ በሚባል ትሪዒት ሕዝቡን እያታለሉ ስግብግብ ከበርቴዎችና ደንታቢስ መንግስቶቻቸው እንዲመዘብሩትና መብቱንና ጥቅሙን በቀጣይነት “የልም ይዣት” አድርገውበት እንዳይዘልቁ አጥብቆ ያምናልም፤ ለለውጥ ይታገላልም። ለዚህም ነው ሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካ ነፃነቱን ከማኅበራዊ ፍትኅ ጋር ሊያቀዳጅ ይችላል ብሎ ያመነበትን ሶሽያል ዲሞክራሲያዊ ርዕዮተ’ዓለም መመሪያው ያደረገው። ወጥነት ያለው ንድፈሃሳባዊ መመሪያ ለአንድ ኅብረተሰብ ሁለንተናዊ ዕድገት አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚያምንና የሶሽያል ዴሞክራሲን ርዕዮተዓለም ደግሞ “ሶሽያሊስታዊ” ከሚባለው/ይባል ከነበረውና “ሊበራል ዴሞክራሲ” ከሚባለው ደግሞ በጎ ጎኖችን ያካተተ በመሆኑ በመመሪያነቱ ይቀበላል። ነገር ግን የማንኛውንም ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ወይንም ሀገር ፖሊሲዎችና የተግባር መመሪያዎች እንዳሉ በመውሰድ (በመቀበል) ኢትዮጵያ ዉስጥ ሊሠራባቸው አይሞክርም፣ ከነግሳንግሱ አንድን ነገር ግልበጣ ትክክልም ሊሆን አይችልም፤ አይደለምም። ከ“አብዮታዊ ዴሞክራሲ” ተብዬው አመለካከትና የፖለቲካ ቀመርም ጋር በምንም መልኩ አይያያዝም። ፓርቲው በሀገራችን፣ ክፍለ-ዓለማችን፣ ተጨባጭ ሁኔታዎች መሠረትና በተጠናና ሕዝብንም ባሳተፈ መልኩ ብቻ ነው የድርጊት መመሪያዎችን የሚያወጣው።

በ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ መጀመሪያ እንደታየው በደርግ ጭፍጨፋ ያለቁትን ምትክ የማይገኝላቸው የአንድ ትውልድ ያህል ልጆቹን ከመገበር አስቀድሞ፣ በነዚያው ትውልድ መታሪዎች ድርጅቱ በህገ-ወጥነት ተፈረጀ። ደርግ ከወደቀም በኋላ በህወሃት/ኢሓዴግ ተመሳሳይ ጭፍጨፋ፣ “የፍየል ወጠጤ ...” የሚለውን የደርግ አጀቢ ዜማ በመተው፣ በለሆሳስ፣ ለዓመታት ተካሄደበት። ከዚያም በላይ ይኸው ዛሬ በአዲሱ ተስፋ-ሰጪ አመራር ወደአገር ግብቶ መንቀሳቀስ እስኪጀምር ድረስ ድርጅታችን በሕገ-ወጥነት እየተፈረጀ በሀገር ዉስጥ በይፋ እንዳይንቀሳቀስ ታግዷል። ከዚህም የተነሳ፣ የኅቡዕ ስራው በጣም አዝጋሚና ደፈር ብለው የሚደራጁትንም ለአደጋ የሚያጋልጥ በመሆኑ ርዕዮቱን በሕዝቡ ዉስጥ፣ የሚሊዮኖችን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ቢሆንም፣ ለማስፋፋት ግን ትልቅ ጋሬጣ ሆኖበት ቆይቷል። ከዚህ አጣብቂኝ ወጥቶ በህጋዊነት መሥራት የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠርም ከዚህ በፊት ቀደም አድርጎና የ1997ቱን ምርጫንም ተንተርሶ አገር ግብቶ ለመንቀሳቀስ ድርጅቱ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ እንደነበረም ይታወቃል።

ኢሕአፓ የሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮት ተከታይ በመሆኑ ከርዕዮታዊ መመሪያው የሚመነጩ ሃሳቦችን፣ መርሆዎችን፣ ዕምነቶችን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ



1. የሶሽያል ዴሞክራሲ ርዕዮተዓለም የህብረተሰቡን በመደቦች መከፋፈል በማመን ከተጨቆኑትና ላባቸውን አንጠፍጥፈው ከሚኖሩት ሠርቶ-አደሮች ጋር ወገናዊነትን የሚያሳይ፣ እንደኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች ደግሞ በግብርናውና ከብት ርቢው መስክ ከተሠማራው ሕዝብ ጋር፤ ለሠፊው ሕዝብ ባጠቃላይ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሥርዓትን ማምጣት ይችላል ብሎ በማመን ላይ የተመሠረተ መመሪያም ነው።
2. በሶሻል ዴሞክራሲ አይዲኦሎጂ የሚመሩ እንቅስቃሴዎች ገና ከጅምሩ ወደ ሶሻሊዝም ምሥረታ የሚደረገውን ጉዞ በሶቭዬት ኅብረትና በሌሎች ሶሽያሊስታዊ ለውጥ አደረግን ባሉ አንዳንድ ሀገሮች በተግባር እንደታየው አብዮታዊ ወይንም ስር-ነቀል በሆነ መንገድና ርምጃዎችም አማካይነት ሳይሆን ሰላማዊና ዝግመታዊ በሆነ መንገድና በርካታ ሕጋዊ ርምጃዎችን በሚያካትት የፖለቲካ ትግል ጉዞ ነው ተፈላጊ ለውጦችን ለማምጣት የሚፈልጉት፤ የሚሠሩትም፤
3. ሶሽያል ዴሞክራሲ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን ደምስሦ በሌላ ወይንም ሶሽያሊስታዊ በሚባል በመተካት ሳይሆን የመንግሥትን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ሚና ኢኮኖሚው ዉስጥ እምብርት በሆኑ ተቋማት ላይ አጉልቶ የካፒታሊስት ኢኮኖሚው ዝንፈቶቹን በሕግ የሚገታበት/የሚሻሽልበት፤ የገበያ ኤኮኖሚን መሠረት ሳያናጋ ነገር ግን ኤኮኖሚው በሞኖፖሊ ካፒታሊስቶች ቁጥጥር ስር ውሎ የጥቂቶች መበልጸጊያና የብዙሃን መበዝበዣ እንዳይሆን የሚከላከል ሁኔታን በመፍጠር ነው ኢኮኖሚያዊ ፍትኅን ለመጠበቅና እንዳይዛባም ለማድረግ የሚጥረው፤
4. በፖለቲካው ዘርፍ በምርጫ የሚመጣ የፖለቲካ ሥልጣን ርክክብን፣ በነፃነት የመድበለ-ፓርቲ ውድድርና ተሳትፎ የሚደረግበት፤ ነፃና ርትዓዊ በሆነ ምርጫ ህዝብ ተወካዮችን የሚመርጥበትን ዴሞክራሲ የሚያምን ስርዓት ነው፤
5. ነጻነትን፤ እኩልነትን፤ ማሕበራዊ ፍትህንና ወንድማማችነት/እህትማማችነትን የሥርአቱ ዋልታዎች በማድረግ ተፈጻሚነታቸውንም በህግ ቀርጾ ማናቸውም ዜጋ በዕምነቱ፤ በአመለካከቱ፤ በተፈጥሮ በደረሱበት/ባት ጉድለቶችም ሆነ በማሕበራዊ የስብስብ ምርጫው/ዋ የዘር፤ የጾታ፤ የዕድሜ፤ የአካለ-ስንኩልነት፤ የዕምነት፤ የድርጅት፤ የብሔር፤ ወ.ዘ.ተ መድልዎ ኢላማ እንዳይደረግ በሕግ የሚከላከልም ርዕዮት ነው።

6. በሶሽያል ዴሞክራሲ ርዕዮተ’ዓለም የሚመሩ መንግሥቶች “የእንክብካቤ መንግሥቶች” (በእንግሊዝኛው የተለምዶ አጠራር-‘ዌልፌር ስቴትስ’)የሚያሰኛቸው በእርግጥም ለዜጎች እንክብካቤ የቆሙ በመሆናቸው ነው። እንዲያውም ዋናው መለያቸው ህብረተሰቡ ዉስጥ በማንኛውም ምክንያት መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ያልቻሉትንና የማይችሉትን ሰብአዊ ክብራቸው ተጠብቆላቸው ፍላጎቶቻቸውም እንዲሟሉላቸው ማድረጋቸው ነው። ይህም ማለት ለህፃናት፣ ለአመጫቶች፣ ለሽማግሌዎች፣ ለ’አካለ-ስንኩላን፣ ለሥራ አጦች፣ ለህሙማን፣ ... ወ.ዘ.ተ. ለሁሉም እንደሁኔታው ልዩና ተመጣጣኝም የሆነ ክብካቤ ለማድረግ/ ለመስጠት የተቃኙ ፖሊሲዎችን ነው የሚያራምዱት። ሁሉም በሾያል ዴሞክራሲ የሚመሩ ሀገሮች ትምህርት በተለይም ሁለተኛ ደረጃን እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ለሁሉም ዜጋ በነጻ የመስጠት ፖሊሲ ነው ያላቸው። የህክምና አገልግሎት ከልደት እስከሞት ድረስ ለሁሉም በነፃ፣ ወይንም አንዳንዶቹን/ችሎታው ያላቸውን የእነሱንም አቅም በማይፈታተን መልኩና በጣም ዝቅተኛ በሆነ ክፍያ፣ ለሁሉም ዜጋ የሚሰጥ ፖሊሲ ነው የሚከተሉት። የ’አካል ጉዳት የደረሰባቸንና ሽማግሌዎችንም ሥርኣት ባለው መንገድ እንዲጦሩ ያደርጋሉ።
7. ምንም እንኳን ሶሽያል ዴሞክራሲ እንደ ርዕዮተ’ዓለም በሚያድግበት ወቅት፣ የምንኖርበትን ዓለምና በተለይም አካባቢያችንን ከውድመትና ብክለት ተከላክሎ ጤናማ መኖሪያችን ማድረግና ለለጣቂ ትውልዶችም በጤናማነቱ የሚተላለፍ ማድረግ አንገብጋቢ ጥያቄ ያልነበረ ቢሆንም፣ ዛሬ ግን ችግሩ አፍጥጦ ስለሚታይ፣ የተፈጥሮ ከባቢን/Environment የሚንከባከቡና ከብክለትና ውድመት የሚከላከሉ ፕሮግራሞችን እያወጡ በግንባር ቀደምነት ለጉዳዩ የሚፋለሙ እነዚሁ በሶሽያል ዴሞክራሲ የሚመሩት ሃይሎችና ሀገሮች ሆነዋል። በመጨረሻም፤
8. ከሶሽያል ዴሞክራሲ መርሆዎች አንዱ “መደጋገፍና መረዳዳት” (ሶሊዳሪቲ) ነውና ይህ መርህ በአንድ ሀገር ወይም በአንድ ድርጅት ዉስጥ በሉዓላዊነት መርህ የሚወሰንና የመጨረሻ ተደርጎ መታየትም የለበትም። መነሻው ይህ ቢሆንም፤ መድረሻው ግን ከተጠየቀ የሕዝበ-ውሳኔ ይሆናል። በርግጥ የሶሽያል ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም ቅንጅት ሥልጣን በሚይዝበት ሀገር ውስጥ ከሀገሪቱ ዜጎች መሐከል በተለያዩ ምክንያቶች “ክብካቤ” የሚገባቸውን ክፍሎች ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም ግን የሶሽያል-ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም ከአነሳሱ ጀምሮ አድማሰ-ሰፊና ዓለም-አቀፋዊ ነው። የሶስተኛው ኢንተርናሽናል አመሠራርትና ግቡም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በማሰብ ነበር።



የማንኛውም ሀገር ሕዝብ በውስጡ በተለያዩ መደቦች የተከፋፈለ ነው። ሰፊው ምዝብርና ለበደልም የተጋለጠው ክፍል ደግሞ በተለያዩ የዕለት ከዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ በሚሠማራባቸው ሥራዎችም የሚጠመድ በመሆኑ መብቱን፣ ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለማስጠበቅ በሙያ ማህበሮች ሳይወሰን በፖለቲካ ድርጅት ደረጃም ተደራጅቶ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች መብቱን እንዳይገፉት፣ ጥቅሙን እንዳያስቀሩበት የመሻሻልና የማደግ ፍላጎቱንም እንዳይቀጩበት ሊያደርግ ይገባዋል።

V. <u>ኢ.ሕ.አ.ፖ እንደ ዋናው የኢትዮጵያ ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መጠናከር አለበት</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የኢትዮጵያ ህዝብ ከራሱ ገዢዎች ግፍና ጭቆና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተላቅቆ ፍትሃዊ ሥርዓትን ለማምጣት ሲያደርግ በቆየው ሃገራዊ ትግል ውስጥ ከሠራተኛው፤ ከተማሪው፤ ከምሁሩና በጠቅላላም ከአገር ወዳዱ ወገን ተውጣጥቶ በአጼ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት ማህጸን ውስጥ ተጸንሶና ተወልዶ አምባገነኑ ወታደራዊ የደርግ ሥርዓት ደግሞ የህዝቡን ሥልጣን በይፋ በእጁ ከማስገባቱ አንድ ወር አስቀድሞ ማለትም በነሐሴ 1967 ዓ/ም የራሱን ህልውና ለህዝብ ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ነው። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት የወለደው ድርጅት ነው።

እንደ ኢትዮጵያውያን ያለ በጣም ታታሪና ኩሩ፣ ታሪኩና የባህል ቅርሱም ስለ ትልቅነቱ የሚመሰክሩለት ለጥቁር ዘር(ሬስ) ምሳሌነት ያለው ሕዝብ፣ አሁን ደግሞ ብዛቱም እየጨመረ በመምጣቱ በተለይ በአፍሪካ ዉስጥ ሊጫወተው የሚችለው ሚና እያጎላ ሊመጣም የሚችል ሕዝብ፣ እስከዛሬ የሚመጥነው፣ የራሱ የሆነ መንግሥትና ሥርዓትን አላገኘም። ሕዝቡ ይህን ለማድረግ ሳይታጋ ቀርቶ አይደለም፣ ያለጥርጥር ታግሏል፣ ከባድ መስዋዕትነም ከፍሏል፣ እስካሁን ግን ፍትኃዊ ሥርዓትን ማምጣት የሚያስችለውን የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ግን አልቻለም። ለምን ብለን መጠየቅና መልሱንም ማግኘት አለብን። ነፃ ሆነን ማሰብ፣ ሁኔታዎችን መመርመርም በጣም ያስፈልገናል። ያለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ በብርቱ ሠራተኛነቱ የሚታወቅ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ውርደትንና የበታችነትን የማይቀበል፣ ብልህ ሕዝብ ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ በነበሩት ሥርዓቶች ሥር ግን የመብቱና የሥልጣን ባለቤት ለመሆን ሳይበቃ ነው ያለው። አብዛኛው ሕዝብ ሙሉውን ቀርቶ አብዛኛውን የጉልበቱን ውጤት የራሱ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታና ሥርዓት ሳያገኝ ነው የኖረው።

ፓርቲ ተገንጥሎ የኮሙኒስት እንቅስቃሴ ጀመረ፣ አሁን የግራው ፓርቲ ወይም በሀገሩ አጠራር "ሴንስተር" የሚባለው ነው። ውሎ-አድሮ እሱም ራሱ "የግራው ጥምረት" እሚባል ዉስጥ "ግሪን" ፓርቲውና ከሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ጋር አብሮ ይሠራል። መጀመሪያ ትልቁን ትግል ያደረጉት ሁሉም ዜጋ የመምረጥ መብት እንዲኖረው ለማድረግ ነበር። በ 1918 ስዊድን ውስጥ ሁሉም ዜጋ የመምረጥ መብት እንዲቀዳጅ ለማድረግ ስለተቻለ በ1920 ዓ.ም ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ስዊድን ዉስጥ ሶሽያል ዴሞክራቶች መሪ የነበረው ግለሰብ፣ የሀገሪቱን መንግሥት የመምራት ዕድል ያገኘው። ምንም እንኳን ፓርላማ ዉስጥ ፓርቲው አብዛኛውን መቀመጫ ባያገኝም፣ ትልቁን ድርሻ ስላገኘ፣ ከሌሎች ጋር በመጣመር ነው ፓርቲው የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ የቻለው።

ስዊዲሽ ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሠራተኞች በሠራተኛ ማህበር ተደራጅተው የፓርቲው ትልቅ ሕዝባዊ መሠረት ሆነው እንዲቆዩ አድርጓል። እስከዛሬ ድረስ አንዱን ከሌላው ለመለየት በጣም አስቸጋሪ በሆነ ደረጃ ነው ትስሥራቸው። ወጣቱንም በወጣት ማህበር አደራጅቶ ከፓርቲው ጋር በተሳሰረ መልክ ይሠራሉ። እነዚህ ሁለቱ ክፍሎች፣ ሠራተኛውና ወጣቶች፣ በተደራጀ መንገድ ነው ከፓርቲው ጋር ተሳስረው የሚሠሩት። የስውድኑ ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ በሕዝባዊ ድርጅቶች መቋቋምና እነሱም ለጥቅማቸው ከሚሟገትላቸው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር መወገን እንዲሚገባቸው ያምናል፣ በተግባርም ደረጃ ይሠራበታል።

የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ተደራጅተው የሚመለከታቸውን ጥያቄ ሊያነሱና ሊታገሉም ይገባል። ነገር ግን <u>የሁሉም ጥያቄዎች ፍትሃዊነት ባለው መልክ የሚፈቱት</u> በሶሽያል ዴሞክራቲክ ፖለቲካ ድርጅት መልክ ተሰባስበውና ሃይላቸውንም አስተባብረው ሲታገሉ ብቻ ነው። በተናጠል የሚገኙ ትንንሽ ድሎች ቢኖሩም የሁሉንም ጥያቄ ዘላቂነት ባለው መልክ ለመፍታት የሚቻለው ግን አጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓቱን በሶሽያል ዴሞክራሲ ርእዮት ለመምራት የሚያስችል ሁኔታ ሲፈጠር ነው። ለሚመዘበሩት ሠርቶ-አደሮችና ህብረተሰቡ ዉስጥ በተለያዩ ምክንያቶች በደልና ግፍ ሊፈጸሙባቸው ለሚችሉት ጥብቅና የሚቆም ፓርቲ ያስፈልጋል። ከእነሱ ጋርም በመወገን፣ በመተሳሰርም ወጥነትና ተዛማጅነት እንዲሁም ቀጣይነት ባለው መልክ ጥያቄዎቻቸውን የራሱ አድርጎ ሊታገል የሚችልም ፓርቲ ሊሆን ይገባል። የዚህ ዓይነቱ ፓርቲ ከሌለ በየጊዜው የሚገኙትን ትንንሽ ድሎች ወደ ዘላቂ መንግሥታዊ ፖሊሲ በመለወጥ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ያዳግታል።



<u>IV.ሶሽያል ዴሞክራሲን መመሪያው ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊነት</u>

ሶሽያል ዴሞክራሲ ልክ እንደ ሌሎቹ በዓለማችን ዉስጥ በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች አድገው የሥርዓት መመሪያዎች ለመሆን እንደበቁት ርዕዮቶች፣ ማለትም እንደ ሊበራል ዴሞክራሲና እንደ ሶሽያሊዝም (ማርክሲዝም) አውቀትና አምኖም ተቀብሎት፣ አብራርቶ የሚገልጠው፣ የሚያስፋፋው፣ ከተፃራሪዎችና ከአውገርጋሪዎች የሚከላከልለት፣ በትክክልና ባግባቡም እንዲተረጎም የሚያደርገው፣ ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር አብሮ ማደግም ሲኖርበት አስፈላጊ የሆነውን የዕድገት አቅጣጫ የሚሰጠው አራማጅ ድርጅት ያስፈልገዋል። በማንኛውም ኅብረተሰብ ዉስጥ ግለሰቦችና የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች መብታቸውን፣ ጥቅማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ከፊታቸው የተደቀኑ የግልና የቡድን ችግሮቻቸውን ያውቃሉ፣ ይገልጣሉ። ታዲያ መብታቸውን ለማስከበር፣ ጥቅማቸውን ለመጠበቅ፣ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዳይችሉ የሚያደርጉ በተፃራሪ ወገኖች አማካይነት የሚደነቀሩባቸው መሰናክሎች ስለሚኖሩ እንዚህን መሰናክሎች ለማስወገድ ወይንም ለማለፍ ካልተሰባሰቡ፣ ካልተደራጁ፣ ጥያቄዎቻቸውን በአግባቡ ካልገለፁ፣ ሁኔታው ሲጠይቅም ተባብረው ካልታገሉ፤ መብታቸው አይከበርላቸውም፣ ጥቅማቸው አይጠበቅም፣ ፍላጎታቸውም አይሟላም።

የሠራተኛው መደብ ከፋብሪካ ባለንብረቶችና ቀጣዎሪቹም ከሆኑት ጉልበታሞች ጋር፣ ከዚያም አልፎ የከበርቴዎቹን ጥቅም ለመጠበቅ ከተመሠረተው በሊበራል ዴሞክራሲ የሚመራ መንግሥት ጋርም ታግሎ መብቱን ለማስከበር ጥያቄውን በትክክል ማቅረቡ ብቻ አይበቃውም። ይህ ማለት በሠራተኞች ማኅበር ደረጃም ብቻ ቢደራጁ በቂ አይሆንም፣ ካለመደራጀት የሚሻል ቢሆንም። የተባበሩትን ከበርቴዎችና መንግሥታቸውን ሊቋቋሙ በሚችሉበት ደረጃ መደራጀት በግድ ያስፈልጋቸዋል። የሠራተኞች የትግል ታሪክ የሚያሳየው፣ ማለትም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። የሠራተኛው መደብ፣ ሌሎችም ሠርቶ-አደሮች፣ መብትና ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ በሠራተኛ ማኅበር ደረጃና ከዚያም በላይ በፖለቲካ ድርጅት መልክ መደራጀት አለባቸው። መንግሥት የሚባለውን ተቋም በሙሉም ሆነ በከፊል በመቆጣጠር የሠርቶ-አደሮችን ጥቅም እንዳይጎዳ፣ እንዲያውም እንዲጠብቅ ለማድረግ በፖለቲካው ሥራ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ድርጅት መኖር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። አካሄዱን ካሳመረ የፖለቲካ ድርጅት ውጤት ማስገኘቱም አይቀርም።

እንደምሳሌ የመጀመሪያውን፣ ከሌሎች ጋር ጥምረት ፈጥሮ በመጋራትም ቢሆን፣ ለፖለቲካ ሥልጣን የበቃ ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እንውሰድ። በጀርመን ውስጥ በ1875 ዓ/ም የተመሠረተው የጀርመን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲም ዕምነት ከርዕዮቱ ዋና ዋና መተክሎችና ብዙ መገለጫዎች ውስጥ ጥቂቶቹና ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ። የዚህ የጀርመን ሶሽያል ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ለበርካታዎቹ መሰል ፓርቲዎች በር ከፋች እንደነበረ መሳት አይገባም።

ኤርፋርት (Erfurt) በምትባል ትንሽ የጀርመን ከተማ ዉስጥ ነበር ፓርቲው መሥራች ጉባኤውን ያደረገውና ፕሮግራሙም በከተማዪቱ ስም ነበር የተጠራው። የፓርቲው ፕሮግራም ብዙ ቁምነገሮችን ከመያዙም በላይ የሠራተኛውን መደብ የፖለቲካ መብት ለማስከበር የተቃኙ በርካታ ነጥቦችን በፕሮግራሙ ዉስጥ አስገብቶ ነበር። (German Social Democracy: The Erfurt Program, 1891) ከዚህ እንደሚከተለው ይላል፤

- ሁሉን ዜጋ በእኩልነት ያሣተፈ፤ ቀጥተኛ የሆነና በምስጢር ድምጽ የመስጠት ሂደት የተደገፈ የምርጫ ሥርዓት ማምጣት፤
- ሕዝቡ የተሣተፈበት የህገ-መንግሥት አቀራረጽ እንዲኖር ማድረግ፤
- የመናገርን፤ የመሰብሰብና ከመሰሎች ጋር የመደራጀት ነጻነት የሚያግዱ ህጎችን ማፍረስ፤
- የሴቶችን መብት ማስከበር፤
- ሃይማኖት የግል ስለሆነ ማናቸውም መንግሥታዊ ድጎማና ማበላለጥ እንዳይኖር ማገድ፤
- ት/ቤቶችን ከሃይማኖት ማላቀቅ፤ ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ እንዲኖር አድርጎም መማር ግዴታ እንዲሆን፤ ትምህርት በነጻ እንዲሰጥ ማድረግ፤
- በህዝብ በተመረጡና ከመንግሥት ተጽእኖ ነጻ በሆኑ ዳኞችና ሠራተኞች የሚተዳደር የፍትህና ለጉዳተኞች የካሣ ሥርዓት መገንባት፤ የሞት ፍርድን ማስቀረት፤
- ነጻ የጤና አገልግሎት ሥርዓት እንዲኖር፤ መድኃኒት በነጻ እንዲታደልና ቀብርም በነጻ እንዲከናወን ማድረግ፤
- ቀስ በቀስ በደረጀና በአቅም ላይ የተመሠረተ የገቢ ታክስ እንዲኖር ማድረግ፤ ማናቸውንም ሌሎች ታክሶችና የጉምሩክ ቀረጦች ማስቀረት ሲሆኑ፤ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች ለማከናወን ደግሞ የሚከተሉት አምስት ርምጃዎች መወሰድ እንደሚኖርባቸው ይገልጻል።

1. ጠንካራና ተፈጻሚነትም የሚኖረው ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ የሆነ የሠራተኛውን መደብ መብት የሚያስጠብቅ ህግ ማውጣትና ይህም ህግ፦
   - የሥራ ሰዓት ከ 8 ሰዓት እንዳይበልጥ የሚያደርግ፤
   - ህጻናት ተቀጥረው እንዳይሠሩ የሚከላከል፤
   - ሠራተኛው ቢያንስ በሣምንት ለ36 ሰዓቶች እንዲያርፍ የሚያደርግ፤

2) መንግሥት የፋብሪካዎችን አሠራር፤ የሠራተኞች ደህንነት (Safety) ጉዳዮችንና የሠራተኛውን መብት በተመለከተ መቆጣጠር፤ መከታተልና ማስከበር እንዲችል ማድረግ፤
3) በእርሻ ሥራ የተሠማሩም ሆኑ በቤት አገልጋይነት የተቀጠሩ ሠራተኞች መብት ልክ እንደ ፋብሪካ ሠራተኞች ሁሉ መብታቸው እንዲከበርላቸው፤
4) የሠራተኛው የመሰባሰብና የመደራጀት መብት እንዲከበር ማድረግና በመጨረሻም የኢምፒሪያል
5) መንግሥቱ (የጀርመን) የሠራተኛውን ሶሻል ኢንሹራንስ ከግል ኩባንያዎች ተረክቦ እንዲያስተዳድር የሚጠይቅ ነበር፤ (Russell, pp.137-141) (4)

እንግዴህ ተመልከቱት የጀርመን ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ከዚህ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ከሠራተኛው መደብ፣ ባጠቃላዩ ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅምና መብት አኳያ ከፍተኛ ግምት የሚሠጣቸው፣ ጥያቄዎች በፖለቲካ ፕሮግራም ነጥቦች መልክ የቀረፀው፣ እንደ አውሮፓያኑ አቆጣጠር በ 1875 ዓ.ም፣ ማለትም ከዛሬ ነበር።

የስዊደን ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ የተመሠረተው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ 1889 ዓ.ም. ነው። ይህ ፓርቲ ሠራተኛው በፖለቲካ ፓርቲ ደረጃ ብቻ ሳይሆን እንደሠራተኛ መደብም ጭምር ተደራጅቶ ጥቅሙን እንዲጠበቅ ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ በማመኑ "ስዊዲሽ ትሬድዩንየን ኮንፌዴሬሽን" (በተለምዶ ኤል ኦ ወይንም ሌበር ኦርጋኒዜሽን) የሚባለው እንዲመሠረት ተባበረ፣ አደረገ ለማላት ሁኔታዎች ስለማያስችሉ። በ 1917 ነበር የስዊዲሽ ሶሽያል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ከከበርቴዎች ጋር በጥምር-መንግሥት ዉስጥ ለመሳተፍ የቻለው። በዚህም የተነሳ የፓርቲው የወጣት ድርጅት "እንዴት ከከበርቴዎች ጋር አብረን እንሠራለን" በሚል ከዋናው